የሰ/መ/ቁ. 95338

ሚያዝያ 12 ቀን 2007 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-**አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ሡልጣን አባተማም

ሙስጠፋ አህመድ

ተኽሊት ይመሰል

**አመልካች፡-**አቶ በቀለ ማሞ - ጠበቃ ደረጀ ታደሰ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-**

1. ሲ/ር ራሄል ብርሃኑ - ቀረቡ
2. ወ/ሮ የሺሀረግ ብርሃኑ - ተወካይ እንደሻው ብርሃኑ ቀረቡ
3. ዶ/ር ዮሴፍ ስዩም - የቀረበ የለም
4. ወ/ሮ ጥሩወርቅ መክቴ - የቀረበ የለም

**መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡**

## ፍ ር ድ

አመልካች በዚህ መዝገብ አቤቱታ ያቀረቡት ባለቤታቸው የነበሩት የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ፈቃድ እና ዕውቅና ውጪ በጋብቻ ውስጥ የተፈራውን የጋራ ቤት ለ2ኛ እና ለ3ኛ ተጠሪዎች በማስተላለፍ፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም በተራቸው ለ4ኛ ተጠሪ በማስተላለፍ የፈጸሙት የሽያጭ ውል እንዲፈርስ እና አመልካች ቤቱን እንዲረከቡ ይወሰንልኝ ሲሉ ያቀረቡት ክስ የመጀመሪያውን የሽያጭ ውል በተመለከተ ክሱ በአዋጅ ቁጥር 213/1992 በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 69(2) መሰረት በይርጋ የታገደ ነው፣የመጀመሪያውን የሽያጭ ውል በተመለከተ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ከሆነ ደግሞ ከሳሽ በ4ኛ ተጠሪ ላይ በተናጠል ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም፣ከሳሽ ድርሻቸውን መጠየቅ የሚችሉት ከ1ኛ ተጠሪ ነው በማለት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናው ብይን መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ አመልካች በ18/12/2004 ዓ.ም. አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ በድሬዳዋ ከተማ በቀበሌ 02 ክልል ውስጥ 250 ካ.ሜ. ይዞታ ያለው እና በካርታ ቁጥር መል/2600 የሚታወቀው ቤት የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ሀብት መሆኑን፣የቤተሰብ ሕጉን እና የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎችን በሚቃረን ሁኔታ የአመልካችን ፈቃድ ሳያገኙ 1ኛ ተጠሪ በ21/04/2002 ዓ.ም. በተደረገ ውል እህታቸው ለሆኑት 2ኛ ተጠሪ እና የ2ኛ ተጠሪ ባለቤት ለሆኑ 3ኛ ተጠሪ በብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ) መሸጣቸውን፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎችም በተራቸው በ26/03/2004 ዓ.ም. በተደረገ ውል ለ4ኛ ተጠሪ በብር 640,000 (ስድስት መቶ አርባ ሺህ) መሸጣቸውን ገልጸው ውሎቹ ከአመልካች ፈቃድ ውጪ እና ተገቢውን ፎርማሊቲ ሳያሟሉ የተደረጉ በመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69(1) መሰረት እንዲፈርሱ መጠየቃቸውን፣1ኛ ተጠሪ በ30/12/2004 ዓ.ም. በሰጡት መልስ ከአመልካች ጋር ከ1982 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1991 ዓ.ም. ድረስ በጋብቻ ኖረው አመልካች

ከኢትዮጵያ ውጪ ከሄዱበት ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ ግንኙነታቸውም መቋረጡን፣ጋብቻቸውም በ1996 ዓ.ም. በፍርድ ቤት ውሳኔ መፍረሱን፣ቤቱንም  አመልካች ከአገር ከወጡ በኃላ ነገር ግን ጋብቻው ከመፍረሱ  በፊት በግል ድካም እና ጥረት ያገኙት የግል ሀብት እንጂ የጋብቻ ውጤት አለመሆኑን፣ሽያጩ የተከናወነው ጋብቻው ከፈረሰ በኃለ በመሆኑ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69 (1) ለጉዳዩ አግባነት የሌለው መሆኑን፣አግባብነት አለው ቢባል እንኳ ክሱ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69(2) እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38126 በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፣የአመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የመጨረሻ ግንኙነት አደረግን ከሚሉበት ከ08/06/1994 ዓ.ም. ጀምሮ ክሱ እስከ ቀረበበት ጊዜ ድረስ አስር ዓመት ያለፈው በመሆኑ ክሱ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1677 እና 1845 ድንጋጌዎች መሰረት በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፣2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በ30/12/2004 ዓ.ም. በሰጡት መልስ የቤተሰብ ሕጉን አንቀጽ 69(2) እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38126 የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ጠቅሰው ክሱ በይርጋ ውድቅ እንዲደረግ መከራከራቸውን፣4ኛ ተጠሪ በ30/12/2004 ዓ.ም. በሰጡት መልስ አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያለቸው መሆኑን ስላላረጋገጡ ክሱ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) መሰረት እንዲዘጋ መጠየቃቸውን፣ክሱ በተሰማበት ጊዜም አመልካች ሌላ ትዳር ከመሰረቱበት ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ ክሱን በአስር ዓመት ውስጥ ስላላቀረቡ ክሱ በአስር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት 1ኛ ተጠሪ መከራከራቸውን እና ፍርድ ቤቱም በመጀመሪያ ደረጃ የመቃወሚያ ነጥቦች ላይ ክሱን ከሰማ በኃላ ይዘቱ ከላይ የተመለከተውን ብይን መስጠቱን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች አከራካሪውን ቤት ከቀድሞ ባለቤታቸው ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኃላ 1ኛ ተጠሪ መሸጣቸው አግባብ ስላልሆነ በአጠቃላይ የተፈጸመው የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት ክስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69(2) ድንጋጌ መሰረት በይርጋ ይታገዳል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. ክርክር ያስነሳውን ቤት ከአመልካች ጋር በተግባር ከተለያየን በኃላ በግል ጥረቴ እና ደካሜ ያፈራሁት የግል ሀብቴ እንጂ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት 1ኛ ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ያቀረቡት የክርክር ነጥብ ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ በማለት  አመልካች ያቀረቡት ክስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69(2) ድንጋጌ መሰረት በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
3. በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) መሰረት አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያለቸው መሆኑን አላረጋገጡም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ  ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ክርክር ያስነሳውን ቤት አመልካች ከአገር ከወጡ በኃላ ነገር ግን ጋብቻው ከመፍረሱ  በፊት በግል ድካም እና ጥረት ያገኙት የግል ሀብት እንጂ የጋብቻ ውጤት እንዳልሆነ በመግለጽ 1ኛ ተጠሪ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከራከሩ ቢሆንም አከራካሪው ቤት ጋብቻው ጸንቶ ባለበት ጊዜ የተፈራ በመሆኑ እና ከፍቺ ውሳኔ በኃላም የጋራ ንብረት ተጣርቶ ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 62 እና 63  መሰረት የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ ግምት የሚወሰድበት መሆኑን እና 1ኛ ተጠሪም ለዚህ ግምት ተቃራኒ የሆነ ሁኔታ ስለመኖሩ አለማስረዳታቸውን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በብይኑ ላይ በግልጽ በማስፈር በዚህ ረገድ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ  ማድረጉን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ይህም አከራካሪው ቤት የ1ኛ ተጠሪ የግል ሀብት እንዳልሆነ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ያሳረፈበት መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡1ኛ ተጠሪ በዚህ ረገድ በተሰጠባቸው ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ያቀረቡት ይግባኝ ስለመኖሩ ወይም ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡት መስቀልኛ ይግባኝ ስለመኖሩ የመዝገቡ ግልባጭ አያመለክትም፡፡በዚህ ሰበር ደረጃም ያቀረቡት መስቀልኛ አቤቱታ የለም፡፡ቤቱ በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ በተሰጠው የብይኑ ክፍል ላይ 1ኛ ተጠሪ ያቀረቡት ይግባኝ ወይም መስቀልኛ ይግባኝ እና መስቀልኛ የሰበር አቤቱታ ከሌለ ደግሞ ክርክር ያስነሳውን ቤት ከአመልካች ጋር በተግባር ከተለያየን በኃላ በግል ጥረቴ እና ደካሜ ያፈራሁት የግል ሀብቴ እንጂ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ንብረት አይደለም በማለት 1ኛ ተጠሪ በሰበር መልሳቸው ያቀረቡት የክርክር ነጥብ ሕጋዊ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚችል አይደለም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በ1982 ዓ.ም. ጋብቻ ፈጽመው እስከ 1991 ዓ.ም. አብረው ከኖሩ በኃላ አመልካች ከኢትዮጵያ ውጪ መሄዳቸው፣1ኛ ተጠሪ ጋብቻው እንዲፈርስ አቤቱታ አቅርበው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 21055 በ26/11/1996 ዓ.ም. የፍቺ ውሳኔ መሰጠቱ፣1ኛ ተጠሪ አከራካሪውን ቤት ለ2ኛ እና ለ3ኛ ተጠሪዎች በብር 30,000 በሽያጭ ያስተላለፉት የፍቺ ውሳኔው ከተሰጠ ከስድስት ዓመታት በኃላ በ21/04/2002 ዓ.ም. በተደረገ ሽያጭ ውል መሆኑ እና 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በተራቸው ቤቱን በብር 640,000 በሽያጭ ለ4ኛ ተጠሪ ያስተላለፉት ከሁለት ዓመታት በኃላ በ26/03/2004 ዓ.ም. በተደረገ ውል  መሆኑ በመዝገቡ የተረጋገጡ ፍሬ ነገሮች ናቸው፡፡በእርግጥ አመልካች ክሱን ሲያቀርቡ 1ኛ ተጠሪ በጋብቻ ወቅት የተፈራውን ንብረት ከአመልካች ፈቃድ ውጪ በሽያጭ ያስተላለፉት ከቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 69(1) ድንጋጌ ውጪ መሆኑን በክሳቸው ላይ ጠቅሰው መከራከራቸውን እና 1ኛ ተጠሪም ለክሱ በሰጡት መልስ ሽያጩ የተከናወነው ጋብቻው ከፈረሰ በኃል በመሆኑ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69(1) ለጉዳዩ አግባነት የለውም በማለት መከራከራቸውን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡በሌላ በኩል እንደ የአግባብነቱ ለክርክሩ አግባብነት አለው ወይም የለውም የሚሉትን ሕግ እና የሕግ ድንጋጌ ጨምሮ ተከራካሪ ወገኖች ይደግፈናል የሚሉትን የየራሳቸውን ክርክር የማቅረብ መብት ያላቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በፍርድ ቤት ለቀረበ አንድ ክርክር ተፈጻሚነት ያለውን ሕግ የመለየት እና ተፈጻሚ የማድረግ ኃላፊነት እና ድርሻ በመሰረቱ የፍርድ ቤቶች መሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡በመሆኑም አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69(1) ድንጋጌ ክርክሬን ይደገፍልኛል በማለት ጠቅሰው ተከራክረው እያለ አሁን በሰበር ደረጃ ደግሞ ይህንን ሀሳባቸውን በመለወጥ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የቤተሰብ ሳይሆን የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች ናቸው በማለት ያቀረቡት  መከራከሪያ በስር ፍርድ ቤቶች ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 329(1) መሰረት ተቀባይነት

ሊሰጠው አይገባም በማለት ተጠሪዎቹ ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለብይኑ መሰረት ያደረገው የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69 የሚገኘው በቤተሰብ ሕጉ የጋብቻ ውጤትን በሚመለከተው ምዕራፍ ሶስት ክፍል ሶስት ስር ሲሆን ይህ ክፍልም ጋብቻው ጸንቶ በሚገኝበት ጊዜ በንብረት በኩል የሚያስከትለውን ሕጋዊ ውጤት የሚገዛ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ 1ኛ ተጠሪ ቤቱን በሽያጭ ያስተላለፉት ጋብቻው እንዲፈርስ በፍርድ ቤት ውሳኔ ካሰጡ በኃላ ሲሆን በቤተሰብ ሕጉ ምዕራፍ አምስት በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰ በኃላ የባልና ሚስቱ ተጣርቶ ውሳኔ ያረፈበት ስለመሆኑም በ1ኛ ተጠሪ በኩል የቀረበ ክርክርና ማስረጃ የለም፡፡1ኛ ተጠሪ ቤቱን በሽያጭ ያስተላለፉት ጋብቻው ከፈረሰ በኃላ ከሆነ ደግሞ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69 (1) "ም" ሆነ (2) ድንጋጌዎች ለክርክሩ ተፈጻሚነት ሊኖራቸው የሚችልበት አግባብ አይኖርም፡፡ አግባብነት ያለው የጋራ ንብረትን ለማስተላለፍ የጋራ በለሀብትን ፈቃድ የሚያስፈልግ ስለመሆኑ በፍ/ሕ/ቁ.1266 የተመለከተው ድንጋጌ ነው ፡፡አንደኛው የቀድሞ ተጋቢ በጋብቻ ውስጥ የተፈራ ነው የሚለውን ንብረት  በተመለከተ ክስ ለማቅረብ የሚችለው ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰበት ቀን ጀምሮ  በምን ያህል ጊዜ ውስጥ እንደሆነ በቤተሰብ ሕጉ ውስጥ በተለይ የተመለከተ ድንጋጌ ባለመኖሩ በዚህ ዓይነት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1677(1) ድንጋጌ መሰረት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ድንጋጌ የተመለከተው አጠቃላይ የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው፡፡በተያዘው ጉዳይ ጋብቻው በፍቺ የፈረሰው በ1996 ዓ.ም. ሲሆን አመልካች ክሳቸውን ያቀረቡት አስር ዓመት ከማለፉ በፊት በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡አመልካች ሕገወጥ ናቸው በማለት እንዲፈርሱ የዳኝነት ጥያቄ ያቀረቡባቸው የሽያጭ ውሎች የተደረጉት ከፍቺ ውሳኔ በኃላ በመሆኑ እና በዚህ ዓይነቱ የዳኝነት ጥያቄም ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ዘመን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 የተመለከተው የአስር ዓመት ጊዜ በመሆኑ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄም በይርጋ የሚታገድ አይደለም፡፡1ኛ ተጠሪ ከአመልካች ጋር የነበረን ግንኙነት የተቋረጠው በ1994 ዓ.ም. በመሆኑ ክሱ በአስር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤት የተከራከሩ ከመሆኑም በላይ በሰበር መልሳቸውም ላይ አመልካች ሌላ ትዳር መስርተው ከሀገር ውጪ እና በሀገር ውስጥ ንብረት አፍርተዋል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጋብቻው የፈረሰው ግራ ቀኙ በተግባር ተለያይተው የየራሳቸውን ኖሮ መምራት ጀምረዋል በሚል የግንኙነት ሁኔታ ሳይሆን በፍቺ ውሳኔ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1846 ድንጋጌ መሰረት የይርጋው ዘመን መቆጠር የሚጀምረው ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰበት ቀን ጀምሮ እንጂ 1ኛ ተጠሪ  ግንኙነቱ በተጨባጭ ተቋርጧል ከሚሉበት ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ አይደለም፡፡ ክርክር ካስነሳው ቤት ውጪ አመልካች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የነበራቸው ጋብቻ ጸንቶ በነበረበት ጊዜ የተፈራ በአመልካች እጅ የሚገኝ ሌላ ንብረት አለ መባሉ 1ኛ ተጠሪን ተገቢውን የመብት ጥያቄ ለማቅረብ የሚያስችላቸው ከሚሆን በቀር ክርክር ባስነሳው ቤት ላይ አመልካች የሚያቀርቡትን የመብት ጥያቄ የሚያስቀረው አይደለም፡፡

የሁለተኛው ጭብጥ ክርክር ሲጠቃለል ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት ክስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69(2) ድንጋጌ መሰረት በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ማናቸውም ሰው ክስ ማቅረብ የማይፈቀድለት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33 (2) ስር የተመለከተ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክሳቸውን በ4ኛ ተጠሪ ላይ ያቀረቡት የጋራ ባለሀብት የሆንኩበትን ቤት ከፈቃዴና እውቅናዬ ውጪ 1ኛ ተጠሪ ለ2ኛ እና ለ3ኛ ተጠሪዎች፣እንዲሁም 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ለ4ኛ ተጠሪ በሽያጭ ያስተላለፉት አላግባብ ስለሆነ ውሎቹ ፈርሰው ቤቱ ይመለስልኝ በማለት ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት በክስ አቀራረብ ደረጃ አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ላይ ጭምር ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያላቸው መሆኑን ከተቀበለ በኃላ በመጨረሻ ግን አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም ከሚል ድምዳሜ ላይ ሊደረስ የቻለው አመልካች በ1ኛ፣በ2ኛ እና በ3ኛ ተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት የውል ይፍረስልኝ ክስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69 (2) መሰረት በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን በምክንያትነት በመያዝ ነው፡፡ቀደም ሲል በሁለተኛው ጭብጥ የውሳኔ ክፍል ውስጥ እንደተገለጸው አመልካች በ1ኛ፣በ2ኛ እና በ3ኛ ተጠሪዎች ላይ ያቀረቡት የውል ይፍረስልኝ ክስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69 (2) መሰረት በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች ተሰጥቶ የነበረው ውሳኔ በዚህ ችሎት የተለወጠ በመሆኑ አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም ሊባል የሚችልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከ4ኛ ተጠሪ የፈጸሙት የሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባዋል ወይስ አይገባውም? የሚሉ እና ተያያዥ ጉዳዮች ደግሞ በግራ ቀኙ ክርክር እና አግባብነት ባለው ሕግ መሰረት በፍሬ ጉዳይ ክርክር ደረጃ በቀጣይ የክርክር ሂደት ውሳኔ የሚሰጥባቸው ይሆናሉ፡፡በመሆኑም በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) መሰረት አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያላቸው መሆኑን አላረጋገጡም በማለት በከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው የብይን ክፍል ሊታረም የሚገባው ነው፡፡

ሲጠቃለል ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት ክስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69(2) ድንጋጌ መሰረት በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት እና በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) መሰረት አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያላቸው መሆኑን አላረጋገጡም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 08233 በ18/08/2005 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 90876 በ04/02/2006 ዓ.ም. በውሳኔ የጸናው ብይን በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ቤት ላይ የተደረገው የሽያጭ ውል ይፍረስልኝ በማለት አመልካች ያቀረቡት ክስ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69(2) ድንጋጌ መሰረት በሁለት ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነው በማለት እና በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) መሰረት አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ያላቸው መሆኑን አላረጋገጡም በማለት የተሰጠው የብይኑ ክፍል ተሽሮአል፡፡

3. አመልካች የይፍረስልኝ የዳኝነት ጥያቄ ያቃረቡባቸው ውሎች የተደረጉት ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰ በኋላ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ዘመን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 የተመለከተው የይርጋ ዘመን እንጂ በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69 (2) የተመለከተው የይርጋ ዘመን አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
4. አመልካች ክሱን ያቀረቡት ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰበት ቀንም ሆነ ውሎቹ ከተደረጉበት ቀን ጀምሮ አስር ዓመት ሳይሞላው በመሆኑ ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
5. አመልካች በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 33(2) መሰረት በ4ኛ ተጠሪ ላይ ጭምር ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡
6. ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በጋብቻ ውስጥ የተፈራ የጋራ ሀብት ነው በሚል የተሰጠው የብይኑ ክፍል አልተነካም፡፡
7. የግራ ቀኙን የፍሬ ጉዳይ ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ እና መርምሮ ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት እንዲመለስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት ወስነናል፡፡
8. በዚሁ መሰረት መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
9. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
10. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

**የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡**

**ሩ/ለ**